# አዝኛለሁ እኔ

## ከድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ

ድሚልኝ ብዕሬ
ብዬ ጀመርኩና
መሪዎች ሊፈቱ
ዘመቻ ሆነና
አወግዘው ገባሁኝ
የእሥር ቤት አፈና
የመሪዎች ሥቃይ
እንዲቆም ፈተና

ለብሼው ሐዘኔን
ናፍቆት ለጤናቸው
አርግዤው ተስፋዬን
ሃሳብ ለነፍሳቸው
መሪዎቼ ወጥተው
መቼ ባየኋቸው
ማየት ብቻ መቼ
መች ልሳለማቸው
ቀናትን ስቆጥር
ኑሩልኝ ልላቸው
የኢትዮጵያ ተስፋ
አሉ እነርሱ ናቸው…

ሕልሜ ቅዠት ሊሆን
ቡዳ ሊበላቸው
የቡዳ መድሃኒት
ፈልጉ በሏቸው
የሕዝባችን ፀሎት
እሱ ይታደጋቸው
እግራቸው ተፈቷል
ኩርፊያውን ይርዳቸው

ኸረ ሰዎች ምነው
አትቆጡም እንዴ
አጥፊም ቢሆን አልሚ
እንክርዳድም ስንዴ
ሸማግሌ አልጠፋ
ነገርን በዘዴ
የውጪ ባላንጣ
መች ገብቶ ወንበዴ
የአገራችን ባህል
ተረስቷል ልማዴ
አመላልስ ገባሁ
የሆዴን በሆዴ

ልማደኛው ልቤ
አትዘን ዘመዴ
ስሜቴም አትጥራኝ
አትቁም ከመንገዴ
እስክመለስ ድረስ
ልጣጥፍ በግዴ
ብዕሬም አትድሚ
እርፍ በል ክንዴ
ሃዘኔን ልጨርስ
ተይኝ ባክሽ ጓዴ

*****  **  *****  **  ******  **  ******

© ድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ
ጥቅምት 2000 (October 2007)
zeaddisu_gebeya@yahoo.com